# የቆሰለ  አንበሳ

ከወያኔ ፍትህ ይገኛል ብላችሁ
እንዳትታለሉ ሚስጥሩ ይግባችሁ።

ከእባብ እንቁላል÷ እርግብ አይገኝም
በቆሎ ተዘርቶ÷ ጤፍ አይታጨድም።

ወያኔና ሻቢያ ባንድ ላይ ተባብረው
ኤርትራን ገንጥለው በኢትዮጵያ ላይ ነግሰው
አበሻን በቋንቋ በጎሳ ከፋፍለው
ታሪኩን አቃለው ባንዲራውን ጥለው
ለግል ዓላማቸው በስውር ተስማምተው
ለኛ የወሰኑት የፍዳ ዘመን ነው።

ወያኔ ሓርነት ብሎ ይነሳና
የትግራይ ሕዝቦችን ያወናብድና
የኢትዮጵያ በር ክፍቱን መሆኑን ያይና
ሰተት ብሎ ገብቶ በቸርችል ጎዳና
ለዚህ አድርሶናል ምኑ ታይቶ ገና።

ጨካኙ ወያኔ የኢትዮጵያ ገዳይ
ጠባብ ትምክህተኛ መሰሪ አታላይ
የሻቢያ ቅጥረኛ የፋሽስቶች ክፋይ
መወገድ አለበት ከትከሻችን ላይ።

ምርጫ ምርጫ ብሎ ሚያሸንፍ መስሎት'
ታጋሹን አበሻ በንቀት አይቶት'
ሕዝቡ እንደተፋው ማወቅ ተስኖት'
የወያኔ ጉዱ ወጥቷል በግንቦት'።

በአዲስ አበባ በዋና ከተማው
የወያኔ ጦር ኀይል በሚቆጣጠረው
በግንቦቱ ምርጫ የተወዳደሩት
ቱባ ቱባዎቹ የኢሕአዴግ ሹማምንት
በዜሮ ሲወጡ ሐቁ ገሀድ ሆኗል
መራጩ ሕዝብ ፈርዷል እውነቱን ተናግሯል
የመለስን ቡድን ገደል ግቡ ብሏል።

ካርዱ ሳይቆጠር አሸነፍኩኝ ካለ
ከዚህ በላይ ቅጥፈት እንግዲህ የት አለ?

ናዚው አቶ መለስ ይብቃዎት ነውሩ
ከዩክሬን ምርጫ ምን አለ ቢማሩ
በጡንቻ እገዛለሁ ከሆነ ነገሩ
ይኸ አያዋጣም ታሪክ ይመርምሩ።

ተቃዋሚውን ኀይል ቢያስሩና ቢገሉ
እናትና ልጆች በጥይት ቢቆሉ
ትግሉ ይቀጥላል መች እንዲህ ይቆማል
ወያኔ ካልጠፋ ሠላም የት ይገኛል።

በኢትዮጵያ አገራችን ብዙ ግፍ ተሰርቷል
የወያኔ ጉድ ግን ከሁሉም ይብሳል።

ዴሞክራሲ ብለን ፍትህ እስካልመጣ
ሠላምን ተጠምተን ሠላምን ሳንጠጣ
ለነፃነት ሞተን ነፃ እስክንወጣ
ወደ ኋላ የለም የመጣው ቢመጣ።

ጀግኖቹ አርበኞች ኢትዮጵያውያኖቹ
የግራዝያኒን ጦር ሰባባሪዎቹ
ለፋሽስት አገዛዝ ምንም ያልተመቹ
ዛሬም ልጆቻቸው ቆርጠን እንነሳ
ለገንዘብ ለንብረት ለሥጋ ሳንሳሳ
ዝም ብሎ አይተኛም የቆሰለ አንበሳ።

የቆሰለ አንበሳ ከተንቀሳቀሰ
በምላሱ ቁስሉን ለማዳን ከላሰ
አድኖ ከበላ ሥጋ ከጎረሰ
ኀይልና ጉልበቱን አንዴ ከመለሰ
ወየው ላዳኞቹ ደሙን ላፈሰሱት
ወየው ለዝንቦቹ ክብሩን ለደፈሩት
ወየው ለጅቦቹ ሊበሉት ላሰቡት
ወየው ለጭልፊቶች ከላይ ላንዣበቡት
አንበሳ አንበሳ ነው ቢገሉት ቢያቆስሉት።

ከሣህሉ በቀለ ቶሮንቶ